በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፍትሕና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩት
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Justice and Legal
Research and Training Institute

ቀን 2 ታህሳስ 2013
Date
ቁጥር
Ref. No ፍሕ/ምክ/ኢ/4.15/36

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ለዲላ ዩኒቨርሲቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ
ለሀረማያ ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ
ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
ለደብረብርሀን ዩኒቨርሲቲ
ለሙቱ ዩኒቨርሲቲ

ለሀዋላ ዩኒቨርሲቲ
ለጅማ ዩኒቨርሲቲ
ለመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ
ለጅማጅጋ ዩኒቨርሲቲ
ለመቀሌ ዩኒቨርሲቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
ለሰመራ ዩኒቨርሲቲ
ለወላይታ ዩኒቨርሲቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ
ለአፍሪካ ቤዛ ዩኒቨርሲቲ

ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ
ለወሎ ዩኒቨርሲቲ
ለኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ
ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
ለቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ
ለኒውጀነራሽን ዩኒቨርሲቲ
ለዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ
ለትድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ
ለኒውሚኒሊየም ዩኒቨርሲቲ
ለሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ
ለአልፋ ዩኒቨርሲቲ

ባሉበት

ጉዳዩ፡ - ***የ2012 ዓ.ም የሀግ ትምህርት የመውጫ ፈተና መሰጫ የጊዜ ሰሌዳ ማስተካከያ ይመለከታል፣***

የ2012 ዓ.ም የሀግ ትምህርት የመውጫ ፈተና በኮቪድ 19 ወረርሽኝና በጸጥታ ምክንያት በቁጥር ፍ/ሕ/ም/ሥ/ኢ/4.15/31 በቀን ህዳር 8 /2012 ዓ.ም በተሃፊ ደብዳቤ ላልተወሰነ ጊዜ በድጋሚ ስለመራዘሙ በፌዴራል የፍትህና የህግ ምርምርና ስልጠና ኢንስቲትዩት በኩል መገለፁ ይታወሳል፡፡

ሆኖም የፍትሕና የሕግ ምርምርና ሥልጠና ኢንስቲትዩት፣ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር እናየሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ በጋራ በመሆን ፈተናውን ለመስጠት ዝግጁ ያልሆኑ ዩኒቨርስቲዎች በቀር በአብዛኛው የሕግ ተመራቂ ተማሪዎች ከህዳር 21- ታህሳስ 6 /2013 ዓ.ም ድረስ የ2012 ዓ.ም የተመራቂ መደበኛ ተማሪዎቻቸውን እንደሚቀበሉ እንደሆነና መመረቂያቸውም ጥር 20ዎቹ ላይ እንደሆነ መረጃዎችን ያሰባሰብን በመሆኑ የተመራቂ ተማሪዎች የቅበላ ጊዜ መርሐ ግብር፣ ተማሪዎች ፈተናው ላይ ለመቀመጥ የሚያስፈልጋቸውን የስነልቦና ዝግጅትና የዩኒቨርሲቲዎች ወቅታዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የመውጫ ፈተናው ከታህሳስ 13-16 ቀን 2013 ዓ.ም የሚሰጥ ሆኖ ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ እንዲገለፅ ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡

ስልክ Tel. 011-6-460918
ፋክስ ቁጥር Fax. No. 011-6-451399
ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 30727
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia
ኢ-ሜይል E-mail JLSRI@ethionet.et

Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፍትሕና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩት
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Justice and Legal
Research and Training Institute

ቀን
Date _____
ቁጥር
Ref. No _____

ስለሆነም የ2012 ዓ.ም የህግ ትምህርት የመውጫ ፈተና ከታህሳስ 13-16 ቀን 2013 ዓ.ም እንዲሰጥ የተወሰነ በመሆኑ ቀደም ሲል የተገለፀ ዝርዝር የድርጊት መርሐ ግብር ማለትም

1. የተፈታኞች ምዝገባ ቀደም ሲል በተገለፀው የጊዜ መርሐ ግብር የተጠናቀቀ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተፈታኞች ምዝገባ ጋር በተያያዘ አስፈታኝ ተቋማት ለኤጀንሲውና ለኢንስቲትዩቱ ማሳወቅ ያለባቸውን የክፍያ ሰነድና ሌሎች መረጃዎችን የማሳወቅ ስራን ከታህሳስ 6/2013 ዓ.ም በፊት እንዲያጠናቅቁ፣
2. የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ከመከላከል አኳያ በጤና ሚኒስቴር የወጡ ወቅታዊ መመሪያዎችን ለማስተግበር የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሁኔታዎች በወቅቱ እንዲጠናቀቁና ከኤጀንሲው በሚተላለፍ መልዕክት መሰረት ከወዲሁ የመፈተኛ ክፍሎችና የፈተና አስፈጻሚዎች ዝግጅት እንዲደረግ፣
3. ቀደም ሲል ከተዘጋጀው የፈተና ፕሮፖዛል አንጻር በኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከላከል ምክንያት የሰው ኃይልና የበጀት ለውጥ ካለ ኤጀንሲው ፕሮፖዛሉን በድጋሚ አዘጋጅቶ በሚያቀርበው ሰነድ መሰረት የልዩነት ሂሳቡ በኢንስቲትዩቱ በኩል እንዲፈጽሙ፣
4. ከታህሳስ 10 – 11 ቀን 2013 ዓ.ም የፈተናውን ሚስጥራዊ ደህንነት በማስጠበቅ የፈተና ስርጭትና የፈተና ጣቢያ ኃላፊዎች ቅበላ ይካሄዳል፣ በመሆኑ አስፈታኝ ዩኒቨርሲቲዎች የተሸከረከሪ እና የፀጥታ አካላት ዝግጅት እንዲያደርጉ፣
5. ታህሳስ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ለተፈታኞችና ፈተና አስፈፃሚች ገለፃ ይሰጣል፣ በመሆኑም አስፈታኝ ዩኒቨርሲቲዎች በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችና ሌሎች ምክንያቶች የሚከሰት የፈተና ደንብ መተላለፍን ከወዲሁ ለመከላከል አስፈላጊው ንግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እንዲሰሩ፣
6. ከታህሳስ 13 – 16 ቀን 2013 ዓ.ም ከጥዋቱ 3፡00 - 6፡00 ሰዓት አስፈታኝ የፈተና ጣቢያዎች ፈተናውን በአግባቡ እንዲያስፈጽሙ፣
7. ከታህሳስ 17-18 ቀን 2013 ዓ.ም የመልስ ወረቀት ሚስጥራዊ ደህንነቱ ተጠብቆ ለኤጀንሲው እንዲመለስ፣ እስከ ጥር 02 ቀን 2013 ዓ.ም ደግሞ የቅድመ እርማት ስራ እንዲጠናቀቅና ለእርማት ስራ ተሳታፊዎች ጥሪ እንዲተላለፍ፣
8. ታህሳስ 26 ቀን 2013 ዓ.ም ከጧቱ 2፡30 ሰዓት ለፈተና እርማት ጥሪ የተደረገላቸው አራሚ ባለሙያዎች ለኤጀንሲው ሪፖርት እንዲያደርጉ፣

ስልክ Tel. 011-6-460918
ፋክስ ቁጥር Fax. No. 011-6-451399
ፖ.ሳ.ቁ P.O.Box 30727
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia
ኢ-ሜይል E-mail JLSRI@ethionet.et

Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፍትሕና የሕግ ምርምር እና ሥልጠና ኢንስቲትዩት
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Justice and Legal
Research and Training Institute

ቀን
Date _____
ቁጥር
Ref. No _____

9. ከታህሳስ 26 -ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም የእርማት ስራ ተካሂዶ የውጤት ጥንቅርና ተያያዥ ስራዎች እስከ ጥር 18 ቀን 2013 ዓ.ም ተጠናቀው የተፈታኞች ውጤት ጥር 20/2013 ዓ.ም በኢንስቲትዩቱ በኩል ለአስፈታኝ ተቋማት ይላካል፡፡
10. ባለው ነባራዊ ሁኔታ አስፈታኝ ዩኒቨርስቲዎች ለማስፈተን አመቺ ሁኔታዎች ከሌሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ የድጋሚ ፈተና በልዩ ሁኔታ በማዘጋጀት እንዲፈተኑ ይደረጋል፡፡ ፈተናውን ለመውሰድ የተዘጋጁ ተማሪዎችን በተመለከተ ዩኒቨርስቲያቸው ለማስፈተን እንደማይችል ካረጋገጠ ተማሪዎቹ በመኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ በሚገኝ የፈተና ጣቢያ ከአንድ ሳምንት በፊት አስቀድመው ሪፖርት በማድረግ እንዲፈኑ ሊደረግ ይችላል፡፡

ስለሆነም ከላይ በተገለጸው መሰረት የፈተና አስተዳደር የድርጊት መርሐ ግብር እንዲሻሻልው ሰኔ የተሰጠበት መሆኑን እየገልፅን የሚመለከታቸው አካላትም የፈተና አሰጣጥና ተያያዥ ስራዎችን በማስፈፀም ሂደት ውስጥ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ምክትል ዋና ዳይሬክተር
ሚ/ዴኤታ

ግልባጭ፡
- ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚ/ዴኤታ
- ለሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ
አዲስ አበባ፣

ስልክ Tel. 011-6-460918 | ፋክስ ቁጥር Fax. No. 011-6-451399 | ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 30727 | አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia
ኢ-ሜይል E-mail JLSRI@ethionet.et

Scanned by CamScanner